የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት
Road Safety & Insurance Fund Service

# የሞተር ብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ እና የደህንነት ማስጠበቂያ

# መመሪያ ቁጥር .... /2017.

ሐምሌ/ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

በሀገራችን የሞተር ብስክሌቶች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለህብረተሰቡ አገልግሎት እየሰጡ በመሆኑ አገልግሎት አሰጣጣቸውን ወጥ በሆነ መንገድ መስመር በማስያዝ በህብረተሰቡ ላይ በሞተር ብስክሌት አሽከርካሪዎች አማካኝነት የሚሰጠውን የትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኗል፡፡

በአንዳንድ ክልሎች በከተማዎች እና ከከተማ ክልል ውጭ ባሉ የገጠሩ የሀገራችን ክፍል የባለሞተር ብስክሌት ትራንስፖርት በሰፊው በመለመድ ላይ ነው፡፡ ይህ እንዳዲስ እየተለመደ እና አገልግሎት እየሰጠ ያለ ዘርፍ በብዙ ችግሮች የተተበተበ እና ለተለያዩ የትራፊክ አደጋዎች እና ወንጀሎች መፈፀም ምክንያት እየሆነ ያለ የትራንስፖርት አማራጭ በመሆን ላይ ነው፡፡

የባለሞተር ብስክሌት የትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ ከሚስተዋሉ ዋናዋና ችግሮች መካከል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የሌላቸው እና እድሜያቸው ለማሽከርከር ያልደረሱ ልጆች የሚያሽከረክሩ መሆኑ፣ የተሳፋሪም ሆነ የአሽከርካሪ የጭንቅላት መከላከያ ቆብ አለመጠቀም እንዲሁም ደረጃውን ያልጠበቀ ቆብ መጠቀም፣ ከመጫን አቅማቸው ባላይ ብዙ ሰው እና እቃ ለአደጋ በሚያጋልጥ መልኩ መጫን፣ አንፀባራቂ እና ሌሎች ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎችን አለመጠቀም የመሳሰሉት ተጠቃሾች ናቸው፡፡

በባለሞተር ብስክሌት አሽከርካሪዎች አማካኝነት በህብረተሰቡ ላይ እየተፈፀሙ ያሉና ሊፈፀሙ የሚችሉ የትራፊክ አደጋዎችና ወንጀሎችን ለመከላከልና የተፈፀሙ የትራፊክ አደጋዎችንም ሆነ ወንጀሎችን ለሚመለከተው የፍትሕ አካል አቅርቦ ሕጋዊ እርምጃ ማስወሰድ የሚያስችል አንድ ወጥ የሆነ የአሰራር መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ሚኒስቴሩ ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የሞተር ብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ እና የደህንነት ማስጠበቂያ መመሪያ ቁጥር ….. /2017 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር"** ማለት የትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤
2. **"አገልግሎት"** ማለት የመንገድ ደህንነት እና መድን ፈንድ አገልግሎት ነው፤
3. **"ክልል"** ማለት በህገ- መንግስቱ አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ማንኛዉም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
4. **"ቢሮ"** ማለት በክልል እና ከተማ አስተዳደር የመንገድ ትራንስፖርትን ለመምራት ስልጣን የተሰጣቸው ተቋማት ወይም አግባብ ባለው አካል ስልጣን የሰጣቸው ተጠሪ ተቋማት ናቸው፤
5. **"ኦፕሬተር"** ማለት የንግድ የሞተር ሳይክል ተሽከርካሪ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ተመዝግቦ የሙያ ብቃት የተሰጠው የተሽከርካሪ ባለንብረት ወይም ድርጅት ወይም ሠራተኛን ነው፤
6. **"የብቃት ማረጋገጫ"** ማለት በክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች በሞተር ብስክሌት የትራንስፖርት አገልግሎት ላይ ለሚሰማሩ ማኅበራትና ድርጅቶች የሚሰጥ ማረጋገጫ ነው፤
7. **"ተጠቃሚ"** ማለት ፈቃድ በመውሰድ በግለሰብ፣ በድርጀትና በማህበር ስም በተመዘገቡ ሞተር ብስክሌቶች አማካኝነት በከተማው ውስጥ ለመንቀሳቀስ የሚቀርብ ግለሰብ ወይም ኦፕሬተር ማለት ነው፤
8. **"ዩኒፎርም"** ማለት የአንድን ተቋም ወይም ድርጅት ሞተር ብስክሌት አሽከርካሪ በተለየ መልኩ የሚገልጽ የተለየ የስራ ልብስ ማለት ነው፤
9. **"ብራንድ"** ማለት የአንድን ተቋም ወይም ድርጅት በተለየ መልኩ የሚገልጽ የቀለም ቅብ እና ስዕላዊ መግለጫ ማለት ነው፤
10. **"ሞተር ብስክሌት"** ማለት የጎን ተሽከርካሪውን ሳይጨምር ክበደቱ ከ400 ኪሎ ግራም የማይበልጥ ባለሁለት ጎማ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤
11. **"ተቆጣጣሪ"** ማለት የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎችንና የትራንስፖርት ህጎች መከበራቸውን ለመቆጣጣር አግባብነት ባለው ሕግ ሥልጣን የተሰጠው የትራንስፖርት ተቆጣጣሪ ወይም የፖሊስ አባል ነው፤
12. **"ማህበር ወይም ድርጅት››** ማለት የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰዱ ባለንብረቶች ወይም ኦፕሬተሮች የሚያቋቁሙት ማኅበር ወይም ድርጅት ነው፤
13. **"የማህበር ፈቃድ"** ማለት የንግድ ቢሮ ወይም የንግድ ሚኒስቴር ወይም ሌላ ማህበራትን ለማደራጀት ስልጣን ባለው አካል የተመዘገቡ በማኅበር ተደራጅተው የንግድ የሞተር ብስክሌት ተሽከርካሪ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ለወሰዱ ባለሃብቶች የሚሰጥ የማኅበር ምዝገባ ፈቃድ ነው፤
14. **"የድርጅት ፈቃድ"** ማለት ከንግድ ቢሮ ወይም ከንግድ ሚኒስቴር በሞተር ብስክሌት የጭነት (መልዕክት አቅርቦት) ትራንስፖርት አገልግሎት ለመሰማራት እንዲቻል የሚሰጥ የንግድ ፈቃድ ነው፤
15. **‹‹የትራንስፖርት አገልግሎት"** ማለት በሞተር ብስክሌት አማካኝነት የሚሰጥ ሰዎችን ወይም ዕቃዎችን የማጓጓዝ አገልግሎት ማለት ነው፤
16. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
17. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ የሴትንም ይጨምራል፡፡

3. **ዓላማ**

የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማ የሞተር ብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን ሕጋዊ ስርዓት በማስያዝ ህብረተሰቡ ሁለንተናዊ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንዲጠቀምባቸው ለማስቻል ነው፤

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ የባለሞተር ብስክሌቶች፣ የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ እና አጠቃቀም ላይ እንዲሁም ፍቃድ በሚሰጣቸው ግለሰቦች፣ ማህበራት እና ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የሞተር ብስክሌት የትራንስፖርት አገልግሎት ዓይነት እና አደረጃጀት

## 5. በሞተር ብስክሌት ሊሰጡ የሚችሉ የትራንስፖርት አገልግሎት ዓይነቶች

1. መንገደኞችን በክፍያ ከቦታ ቦታ ማዘዋወር፤
2. በሞተር ብስክሌቱ በተገጠመ የዕቃ ማስቀመጫ ሳጥን ውስጥ የተለያዩ እቃዎችንና መልእክቶችን በክፍያ ማመላለስ፤
3. ለግል የትራንስፖርት አገልግሎት ፍላጎት መጠቀም
4. ክልሎች እና ከተማ አስዳደሮች በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት አገልግሎቶች በሙሉ ወይም በከፊል እንደ ክልሉ ወይም ከተማ አስተዳደሩ ነባራዊ ሁኔታ ተግባራዊ ላያደርጉ ይችላሉ፡፡

6. **የትራንስፖርት አገልግሎት ፈቃድ የሚያገኙ የሞተር ብስክሌቶችን በተመለከተ**

1. በሀገር አቀፍ ደረጃ የሞተር ብስክሌት ምዝገባ በማካሄድ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ የሞተር ብስክሌት ባለንብረቶች በማህበር በመደራጀት በሞተር ብስክሌት የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰማሩ በተመዘገቡበት ክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች የኦፕሬሽን ዘርፍ ፈቃድ ይሰጣቸዋል፤
2. በማህበር በመደራጀት በትራንስፖርት አገልግሎት ለመሰማራት ፈቃድ የሚሰጣቸው ሞተር ብስክሌቶች በኮድ3 ተመዝግበው የሚገኙ መሆን አለባቸው፤
3. አንድ ማህበር አገልግሎት ለመስጠት ሲደራጅ መደራጀት የሚችለው በአንድ የአገልግሎት ዘርፍ ብቻ ነው፡፡

4. እንደ ክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ በተለያየ ምክንያት ሰሌዳ ያላገኙ ሞተር ሳይክሎች ችግር ባለባቸው ክልሎች ሰሌዳ የሌላቸው የሞተር ብስክሌቶችን የሚያቅፉ ማህበራት በሂደት የሚጠበቅባቸውን ግዴታዎች በመወጣት ወደ ህጋዊ መስመር እንዲገቡ ያደረጋል፤

## 7. በሞተር ብስክሌት የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ለማግኘት ሊሟሉ የሚገባቸው መስፈርቶች

### 1. ሰሌዳ ያላቸው በሞተር ብስክሌት የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ለማግኘት ሊሟሉ የሚገባቸው መስፈርቶች

1.1 የባለሞተር ብስክሌት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ያለው፤

1.2 የወቅቱን የ3ኛ ወገን መድን ሽፋን እና የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ (ቦሎ) ማቅረብ የሚችል፤

1.3 በሚኒስቴሩ የተቀመጠውን የሞተር ሳይክል እስታንዳርድ የሚያሟላ እና በየክልሉ አንድ አይነት ቀለም ያለው ሆኖ የቀለሙን ዓይነት ክልሉ ወይም ከተማ መስተዳድሩ ይወስናል፤

1.4 **በዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሱትን አገልግሎቶች ለመስጠት፡**

1.4.1 በክልሎች እውቅና ያለው ማህበር አባል መሆን፤

1.4.2 አንፀባራቂ ዩኒፎርም መለያ መልበስ፤

1.4.3 ለመልዕክት አገልግሎት ወይም መንገደኞችን ለማጓጓዝ ለተደራጁ ከሆነ መንቀሳቀሻ ፈቃድ እና 10 በ 20 የሆነ የደረት ባጅ ማንጠልጠል፤

1.4.4 ለመልዕክት አገልግሎት ከሆነ እንደሞተር ሳይክሉ ዓይነት የተቀባ የእቃ መጫኛ ሳጥን በእስታንዳርዱ መሰረት ማስገጠም፤

1.5 በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን ግዴታዎች ጠብቆ ለመንቀሳቀስ ፈቃደኛ የሆነ፤

1.6 እንደ ክልሉ ወይም ከተማ መስተዳድሩ ተጨባጭ ሁኔታ ተጨማሪ መስፈርቶች ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ክልሎች ወይም ከተማ አስተዳድሮች ማውጣት ይችላሉ፡፡

1.7 ሰሌዳ ያላቸው በሞተር ብስክሌት የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ለማግኘት ሊሟሉ የሚገባቸው መስፈርቶች

1.7.1 የባለሞተር ብስክሌት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ያለው፤

1.7.2 የወቅቱን የ3ኛ ወገን መድን ሽፋን እና የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ (ቦሎ) ማቅረብ፤

1.7.3 በሚኒስቴሩ የተቀመጠውን የሞተር ሳይክል እስታንዳርድ የሚያሟላ እና ሰማያዊ ቀለም የተቀባ ሞተር ብስክሌት ማቅረብ፤

1.7.4 በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀጽ 7. 1 እና 7.2 የተጠቀሱትን አገልግሎቶች ለመስጠት

1.7.4.1 በክልሎች እውቅና ያለው ማህበር አባል መሆን፤

1.7.4.2 ለመልዕክት አገልግሎት ወይም መንገደኞችን ለማጓጓዝ ለተደራጁ ከሆነ ሰማያዊ የሞተር ብስክሌቱን አካል መቀባት እና ሰማያዊ ዩኒፎርም መለያ መልበስ፤

1.7.4.3 ለመልዕክት አገልግሎት ወይም መንገደኞችን ለማጓጓዝ ለተደራጁ ከሆነ መንቀሳቀሻ ፈቃድ እና 10 በ 20 የሆነ የደረት ባጅ መያዝ፤

1.7.4.4 ለመልዕክት አገልግሎት ከሆነ እንደሞተር ሳይክሉ ሰማይዊ የተቀባ የእቃ መጫኛ ሳጥን በእስታንዳርዱ መሰረት ማስገጠም

1.7.5 በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን ግዴታዎች ጠብቆ ለመንቀሳቀስ ፈቃደኛ የሆነ፣

## 8. ባለሞተር ብስክሌቶች የማህበር አደረጃጀት እና የምዝገባ ሂደት

ሁሉም ባለሞተር ብስክሌቶች በሙሉ በትራንስፖርት ዘርፉ ላይ ለመሰማራት እና አገልግሎት ለመስጠት ይችሉ ዘንድ በማህበር መደራጀት ወይም በድርጅት ስር መታቀፍ የግድ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በንግድ ድርጅቶች ወይስ በማህበር ስር ታቅፈው የተለያዩ አገልግሎቶችን ለተለያዩ አካላት የሚሰጡ ድርጅቶች ግልፅ በሆነ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ እና የጉምሩክ የታክስ ግዴታቸውን በአግባቡ የተወጡ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ በማህበር ተደራጅተው የትራንስፖርት አገልግሎት እና እቃ የማድረስ አገልግሎት የሚሰጡ ማህበራት ህጋዊ የሆኑት እና ህጋዊ ያልሆኑት በአንድ ማህበር መታቀፍ አይችሉም፡፡ ህጋዊ ያልሆኑ የሞተር ብስክሌቶችን ያቀፉት ማህበራት በሂደት በጉምሩክ ኮሚሽን እና በትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር በሚያወጡት መመሪያ መሰረት የሚጠበቅባቸውን ግዴታዎች በመወጣት ወደ ህጋዊ መስመር እንዲገቡ ያደረጋል፡፡

## 9. የስራ ልብስ (ዩኒፎርም)

1. በክልሉ የዕቃ እና የሰው ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ሞተር ብስክሌት አንድ ዓይነት የሆነ የስራ ልብስ (ሰማያዊ ዩኒፎርም) ይለብሳሉ፤
2. ዩኒፎርሙ በሌላ መደበኛ ልብስ ላይ በመደረብ የሚለበስ ቀላልና ሰማያዊ ደረጃውን የጠበቀ ዓይነት ሲሆን የምሽት አንፀባራቂ በአግድም የተለጠፈበት ነው፤
3. ዩኒፎርሙ ያልተቀደደ፣ ንጹህ፣ ትክክለኛ ይዘቱን የጠበቀ እና ጀርባው ላይ የሚቀመጠው ጹሁፍ ከርቀት የሚለይ በጉልህ ቀለም የተፃፈ እና የፅሁፍ መጠኑም ከተሽከርካሪ ሰሌዳ የፅሁፍ መጠን ያላነሰ መሆን አለበት፤

## 10. የዕቃ ማስቀመጫ ሳጥን

1. ዕቃ የሚያመላልሱ ሞተር ብስክሌቶች ዕቃውን የሚይዙበት ሳጥን 50 ሳ.ሜ x 46 ሳ.ሜ x 46 ሳ.ሜ ያልበለጠ መጠን እንዲሁም ዝናብ በማያስገባ ሁኔታ በብረት ወይም በፕላስቲክ የተሰራ መሆን አለበት፤
2. የዕቃ ማስቀመጫ ሳጥን ተመሳሳይ እይታ እንዲኖረው በሚያስችል ሁኔታ እንደ ሞተር ብስክሌቱ ቀለም ሰማያዊ በማይለቅ ቀለም መቀባት አለበት፤

## 11. የሞተር ብስክሌት የደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎች ስለመጠቀም

1. የሞተር ብስክሌት አሽከርካሪ ደህንነቱን ለመጠበቅ የሚረዱ ሄልሜት እና ሌሎች የደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎች መጠቀም አለበት፤

2. የጭንቅላት ደህንነት መከላከያ (ሄልሜት) ለሞተር ብስክሌት አሽከርካሪ ተብሎ በኢትዮጵያ ስታንዳርድ መሰረት የተዘጋጀ ብቻ መሆን አለበት፤
3. ወደ ጐን የምትለጠፍ አንፀባራቂ ያለው ልብስ
4. የጉልበት ጉዳት መከላከያ
5. የእጅ ጓንት
6. የደህንነት ጫማ
7. የዓይን መከላከያ መነጽር
8. የዝናብ መከላከያ ልብስ

**12. የፍጥነት ወሰን**

በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር የከተማዋ የሞተር ብስክሌት የፍጥነት ወሰን በደንብ ቁጥር 492/2014 መሰረት መሆን አለበት ነገር ግን ክልሎች ከራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር በማየት ደንብ ላይ ከተጠቀሰው የፍጥነት ወሰን ቀንሰው እንዲያሽከረክሩ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

**ክፍል ሦስት**

**የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ ዓይነት ስለመወሰን**

**13. የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ ዝርዝር መግለጫ**

**በሞተር ሳይክል ላይ የሚገጠመው የመቆጣጠሪያ እና የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ (GPS) ዝርዝር መግለጫ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ዋና ዋና ነጥቦች ማሟላት ይገባቸዋል።**

1. **በየትኛውም ሰዓትና ጊዜ የሞተር ሳይክል እና ኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክል ያለበትን ቦታ እና ሁኔታ (Real time) በግልፅ ሊያሳይ የሚችል መሆን አለበት፤**
2. **በክልልና ከተማ መስተዳድር ትራንስፖርት ቢሮ እውቅና ከተሰጠው የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ አቅራቢ ድርጅት የመቆጣጠሪያ ስርዓት (System) ጋር የተጣጣመ ሊሆን ይገባል፤**
3. **ሞተር ብስክሌት ቢያንስ ሲሄድበት የነበረውን ፍጥነት፣ የተቀንሳቀሰበትን ቀን፣ ሰዓት፣ ዓመት ምህረት እንዲሁም የተንቀሳቀሰበትን አካባቢ ትክክለኛ መረጃ እንዲሁም የነበረበትን ቦታ ማሳየት የሚችልና መስጠት የሚችል መሆን ይገባዋል፤**
4. **ሞተር ብስክሌት በቀላሉ የሚለይበት የራሱ የሆነ የተለየ የመለያ ቁጥር እና ሌሎች መለያ ኮዶች የያዘ መሆን ይገባዋል፤**
5. **ቴክኖሎጂው ቢያንስ በሀገሪቱ ያለውን ዝቅተኛ የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂ መስፈርት ያሟላ መሆኑን ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም የብቃት ማረጋገጫ ሊኖረው ይገባዋል፤**

6. *እያንዳንዱን መረጃ የሞተር ብስክሌት ሙሉ እንቅስቃሴ በማያቋርጥ ሁኔታ በግልፅ የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል፤*
7. *በተለያዩ ምክንያቶች የኃይል መቆራረጥ ቢያጋጥም ወይም ጉዳት ለማድረስ በመሞከር ቢያንስ ለ15 (ለአስራ አምስት) ቀናት ያህል የሞተር ብስክሌቱን ሙሉ እንቅስቃሴ የሚያሳይ እና ማሳወቅ የሚችል መሆን አለበት፣*
8. *በከተሞች አካባቢ ከከፍተኛ የፍጥነት ወሰን 50 ኪ/ሜ በሰዓት በላይ ሲያሽከረክር የቀይ መብራት ማሳየት የሚችል ሆኖ የፍጥነት ወሰኑን ሲያልፍ ቢያንስ ከ 5 ሰከንድ ቆይታ በኃላ ያለማቋረጥ ቀይ መብራት ምልክት በጉልህ እንዲያሳይ ሆኖ የተዘጋጀ መሆን ይኖርበታል፤*
9. *አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የክልል እና የከተማ አስተዳድር ትራንስፖርት ቢሮዎች የሞተር ብስክሌት የጥፋት አመላካች ቀይ መብራት ከቢሮ በመሆን ቀይ እንዲያበራ ማድረግ የሚችል መሆን አለበት።*
10. *በማንኛውም ሰዓት አሽከርካሪው ከተወሰነው የፍጥነት ገደብ በላይ በመንዳቱ ሞተር ብስክሌቱ ቀይ በርቶ ሲያገኝ መጀመሪያ ቅጣቱን በመክፈል በቢሮው በአካል ቀርቦ እንዲጠፋለት ማድረግ አለበት።*
11. *ማንኛውም ማህበር ወይም ድርጅት የመንገድ ቢሮው ውል ከገባባቸው ቴክኖሎጂ አቅራቢ ተቋማት ጋር ብቻ ውል መያዝ እና ማስገጠም አለበት።*

# ክፍል አራት

# የተለያዩ አካላት ኃላፊነት

የባለሞተር ብስክሌት የትራንስፖርት አገልግሎትን በሕጋዊ ሁኔታ ለማስተዳደርና ለመደገፍ የሚመለከታቸው አካላት የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡

## 14.የሚኒስቴሩ ኃላፊነት

1. የባለሞተር ብስክሌትን የሚመለከት መመሪያ ያወጣል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ያሻሽላል ይሽራል፤
2. የአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የቅሬታ አፈታት ስርዓት ይዘረጋል ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋል የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጣል፤
3. የሙያ ማሻሻያ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ያዘጋጃል፣ ያከናውናል፤
4. ሕጋዊ መስመር ለያዙ ባለሞተር ብስክሌቶች የሚሰጠውን ሠሌዳ በበቂ እና በጉልህ በሚታይ መልኩ እንዲመረት፣ እንዲሰራጭ፣ይከታተላል፤
5. የሞተር ብስክሌት ትንስፖርት አጠቃላይ አገልግሎት አሰጣጥ በተመለከተ ጥናቶች በማካሄድ ተሞክሮዎችን በመቀመር በየጊዜው የአሠራር ማዕቀፎችን ያሻሽላል፤

6. የአየር ንብረት፣ የትራንስፖርት አገልግሎትን የመሳሰሉትን ዘመኑ የሚጠይቃቸው መስፈርቶችን ያካተተ የሞተር ብስክሌት ተሽከርካሪ ደረጃ እንዲወጣ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ይሰራል፤
7. በአገልግሎቱ የሚዘጋጀውን የቴክኖሎጅ አቅራቢ ድርጅቶችን መምረጫ መስፈርት ማፅደቅ፤

## 15.የአገልግሎቱ ኃላፊነት

1. ወደ አገልግሎት የሚገቡ ሞተር ብስክሌቶች የግል፣የማህበር እና የድርጅት ንግድ ስራዎች አገልግሎት አሰጣጥ እና አደረጃጀት በተመለከተ ክልሎች እንደ ተጨባጭ ሁኔታቸው የሚመዘገቡበት አጠቃላይ አቅጣጫ የሚሰጥ ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ ያዘጋጃል፤
2. ሞተር ብስክሌት አሽከርካሪዎችና የተገልጋዮች አደጋ መከላከያ ቁሳቁስ እና በምሽት ወቅት በተሻለ እንዲለዩ የሚያደርግ አንፀባራቂ ልብስ እንዲለብሱ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤
3. የሞተር ብስክሌት ትንስፖርት አጠቃላይ አገልግሎት አሰጣጥ በተመለከተ ጥናቶች በማካሄድ ተሞክሮዎችን በመቀመር በየጊዜው የአሠራር ማዕቀፎች ያሻሽላል፤
4. የሞተር ብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓት እንዲኖረው በቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
5. ለተለያዩ አካላት የሙያ ማሻሻያ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ያዘጋጃል ያከናውናል፤
6. ሀገር አቀፍ የሞተር ብስክሌቶች እና አሽከርካሪዎችን መረጃዎች በማሰባሰብ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከታቸው አካላት ማሰራጨት፤
7. በምዝገባና በዕድሳት ጊዜ የባለሞተር ብስክሌት ተሽከርካሪዎች የ3ኛ ወገን መድን ሽፋን እና የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ (ቦሎ) ያላቸው መሆኑን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤
8. ሞተር ብስክሌት አሽከርካሪና ተገልጋዮች ጥቅም ላይ የሚውሉ የራስ ቆብ (ሄልሜት) ደረጃና መመዘኛ (ስፔስፊኬሽን) ያወጣል ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
9. የአየር ንብረትን፣ የትራንስፖርት አገልግሎትንና የመሳሰሉትን ዘመኑ የሚጠይቀውን መስፈርት ያካተተ የሞተር ብስክሌት ተሽከርካሪ ደረጃ እንዲወጣ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ተባብሮ ይሰራል፤
10. የሞተር ብስክሌት ተሳፋሪ ሆነው ሲሄዱ ከአንድ ሰው በላይ አለመጫናቸውን ከክልሎች እና ከተማ መስተዳድሮች ጋር ተባብሮ በመስራት ማረጋገጥ፤
11. ዓመታዊ የምዝገባ እና የፍቃድ እድሳት መስፈርት (ቼክ ሊስት) ያዘጋጃል አፈፃፀሙ ላይ ክትትል እና ድጋፍ ያደራጋል፤

## 16.የክልል እና ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮዎች ኃላፊነት

1. ሞተር ብስክሌት በግል፣ በህዝብ እና በጭነት ማመላለስ እንዲሁም የመልዕክት አገልግሎት የሚሰጡበት አሰራር ደህንነቱ በተጠበቀ፤ ተደራሽ እና ሕግን መሠረት ባደረገ መልኩ አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውን ይከታተላል፤
2. ከክልላቸው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር በማየት ይህን መመሪያ በማይቃረን መልኩ ለሞተር ብስክሌት አገልግሎት አሰጣጥ እና አደረጃጀት ዝርዝር መመሪያ ሊያወጡ ይችላሉ፤

3. በንግድ አገልግሎት ላይ የተሰማሩ የባለሞተር ብስክሌቶች አገልግሎት አሰጣጥን ለማሳለጥ በትራንስፖርት አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ባለንብረቶችን በማህበር በማደራጀትና ፍቃድ በመስጠት፤ ማህበራቱና አባሎቻቸው የሚሰጡት አገልግሎት በዚህ መመሪያ መሰረት ከማሽከርከር ስነ ምግባር ውጪ ከሆነ ወይም በወንጀል ድርጊት ከተሳተፉ ማህበራቱን ለተወሰነ ጊዜ ወይም እስከ መጨረሻ በማገድ በስነ-ምግባር የታነጸና ደህንነቱ የተረጋገጠ አገልግሎት እንዲሰፍን ማድረግ ፤
4. የህዝብ ትራንስፖርት ሰጪ ተሽከረካሪዎች ስምሪት ጋር በማይቃረን መልኩ፤ ለሕዝብ ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ በመስጠት የስምሪት ምድብና መርሀ-ግብር እንዲያወጡ የመደገፍና የማፅደቅ ስራዎችን በማከናወን በታችኛው የአስተዳደር መዋቅር በኩል ተግባራዊ መሆኑን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፤
5. ለሞተር ብስክሌት ብቻ የተወሰኑ ኮሪደሮች ወይም መስመሮች በቋሚነት ወይም በተወሰኑ ሰዓታት በመለየት እንዲንቀሳቀሱ የማድረግ፤ እንዲሁም የሚንቀሳቀሱበትን የመንገድ ክፍል የመከልከልና የመፍቀድ፤
6. በክልል ደረጃ የሚታዩ የህገወጥ የሞተር ብስክሌቶች እና አሽከርካሪዎች መረጃዎች በማሰባሰብ ማስተካከያ እርምጃ የመውሰድ፤
7. የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በሂደት በብቃት መሸፈን የሚቻልባቸውን መስመሮች በመለየት እንደ አስፈላጊነቱ የሞተር ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ እንዳይውል የማገድ፤
8. የሞተር ብስክሌቶች ከቦታው የፍጥነት ወሰን ገደብ አንፃር የሚጓዙበትን ከፍተኛ የፍጥነት ገደብ የመወሰን፤
9. የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ የሞተር ብስክሌቶች ዓመታዊ የቴክኒክ ብቃት ሠርትፍኬት ቦሎ እና ሶስተኛ ወገን ሲያቀርቡ ምዝገባ በማከናወን ፍቃድ ያድሳል በየዓመቱ የምዝገባ ፍቃድ ያላሳደሰ ማህበር ወይም ድርጅት ወይም የሞተር ብስክሌት ባለቤት የትራንስፖርት አገልግሎት እንዳይሰጥ ይከለክላል፣ ተፈጻሚነቱም ይቆጣጠራል፤
10. በትራንስፖርት አገልግሎት ማህበር የተደራጀ ማንኛዉም አባል ወደ ሌላ ማህበር ጋር ለመደራጅት ቢፈለግ ከዚህ በፊት የትራንስፖርት አገልግሎት ከሚሰጥበት ማህበር ሕጋዊ መሸኛ ደብዳቤ (Clearance) ሲያቀርብ ዝውውሩን ይፈቅዳል፤
11. ዓመታዊ የምዝገባ እና የፍቃድ እድሳት ተግባራት በመመዘኛ መስፈርት (ቼክ ሊስት) መሰረት ያከናውናል እንዲሁም የአገልግሎት የቅሬታ አፈታት ስርዓት ይዘረጋል፤
12. **በሞተር ብስክሌት ላይ የተገጠሙ የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂዎች እና የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ በተቀመጠው ዝርዝር መግለጫ መሰረት መሆኑን ያረጋግጣል።**
13. **ጂፒኤስ ስለመገጠሙ፣ ቦሎ ስለማድረጉ እና በማህበር ሞተር ብስክሌቶች የማህበር አባልነት የምዝገባ ማረጋገጫ ሲቀርብ መንቀሳቀሻ ፍቃድ ይሰጣል።**
14. **የመከታተያ ስርዓቱን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ፈቃድ በወሰዱ አካላት ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤**
15. **የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ ለሚያስፈልጋቸው ተጠቃሚዎች የመጠቀም ፈቃድ ይሰጣል፣**

16. የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች ቴክኖሎጂውን በሚያሽከረክሩት ሞተር ብስክሌት ላይ በአግባቡ በመግጠም በክልሉ እና በከተማው ሰላማዊ በሆነ መልኩ መንቀሳቀሳቸውን እንዲሁም በክልሉ እና በከተማው ለማሽከርከር በተፈቀደው የፍጥነት ወሰን እያሽከረከሩ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣
17. የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ ዕቃዎችን ዓይነት፣ ባለቤት፣ ቦታና የመሳሰሉትን መረጃዎች የያዘ መረጃ አደራጅቶ ይይዛል፣
18. በሞተር ብስክሌት የትራፊክ ህጎችና ሌሎች የህግ መተላለፎች ሲፈፀሙ ቴክኖሎጂውን በመጠቀም መረጃዎችን ለሚመለከተው አካል ማቅረብና ባለው ስልጣን እርምጃ ይወስዳል።

## 17.የክልል እና ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን ኃላፊነት

1. ሰሌዳ የሌላቸው ወይም በዚህ መመሪያ መሰረት ተመዝግበው በማህበር ያልተደራጁ ሞተር ብስክሌቶች ወደ መንገድ ወጥተው አገልግሎት እንዳይሰጡ የቁጥጥር ስራ ማከናወን ሕጋዊነታቸው እስከሚረጋገጥ ድረስ እንደ አስፈላጊነቱ በሕግ ቁጥጥር ስር በማድረግ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፤
2. በመንገድ ደህንነት ደንብ ቁጥር …../2016 አንቀጽ 95 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ጥብቅ የደንብ ማስከበር ስራውን አጠናክረው የማስቀጠል፤
3. በዚህ መመሪያና በሌሎች የመንገድ ደህንነት ሕጎችና ደንቦች ስለ ሞተር ብስክሌቶች ፍሰት ደኅንነት የተደነገጉ የትራፊክ ሕጎች እንዲከበሩ የቁጥጥር ስራ ማከናወን፤
4. ሞተር ብስክሌት በመጠቀም የትራፊክ ህጎችና ሌሎች የህግ መተላለፎች ሲፈፀሙ ለሚመለከተው አካል ማቅረብና ባለው ስልጣን እርምጃ መውሰድ፤
5. በተለያዩ የግንዛቤ መንገዶች በመጠቀም ለሞተር ብስክሌት አሽከርካሪዎች ግንዛቤ መፍጠር፤

## 18.የባለሞተር ብስክሌት ባለንብረቶች ኃላፊነት

1. ሕጋዊ የሆነና በትራንስፖርት ቢሮ የተመዘገበ ሠሌዳ በተመዘገበበት የስራ መስክ ብቻ መጠቀም፤
2. ህጋዊ ያልሆኑ ሞተር ብስክሌቶች ባለቤቶች በጉምሩክ ኮሚሽን እና በትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር በሚያወጡት መመሪያ መሰረት የሚጠበቅባቸውን ግዴታዎች በመወጣት ወደ ህጋዊ መስመር የመግባት፤
3. የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ የሞተር ብስክሌት ባለንብረቶች በየመኖሪያ ጣቢያቸው በማህበር በማደራጀት በሞተር ብስክሌት አጠቃቀምና አስተዳደር በተደነገጉ መመሪያዎች መሠረት ብቻ አገልግሎት የመስጠት፤
4. ማንኛውንም ሕገ-ወጥ ድርጊት በሞተር ብስክሌታቸው አለመፈፀሙን እና ለሕገ-ወጥ ድርጊት ተባባሪ አለመሆናቸውን ማረጋገጥ፤
5. በአሽከርካሪዎቻቸው ሕገ-ወጥ ድርጊት መፈጸሙን መረጃ ሲደርሳቸው ወዲያውኑ ለሚመለከተው አካል እና ለማህበራቸው ማሳወቅ፤
6. የሞተር ብስክሌቱ አሽከርካሪና ተሳፋሪ ደረጃውን የጠበቀ የአደጋ መከላከያ ቆብ እና አስገዳጅ የሆኑ የደህንነት ቁሳቁሶች ሲሟሉ ብቻ ለትራንስፖርት አገልግሎት ማዋል፤
7. በሞተር ብስክሌት የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት በቢሮው የተሰጠው ፈቃድ ትራፊክ ተቆጣጣሪ ወይም መደበኛ ፖሊስ ሲጠየቁ የማሳየት፣

8. የሞተር ብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት ፈቃድ ሳይወስዱ አገልግሎት አለመስጠት፣
9. ለሚሰጠው አገልግሎት ደህንነቱ እና ምቾቱ የተጠበቀ የሞተር ብስክሌት ተሽከርካሪ የማቅረብ፣
10. በክልሉም ሆነ በሚመለከተው አካል ሲፈለግ የመቅረብና የአድራሻ ለውጥም ካደረገ የማሳወቅ ኃላፊነት ይኖርበታል፤
11. ሕጋዊ ሂደታቸውን ለጨረሱ ባለሞተር ብስክሌቶች ሠሌዳ መቀበልና በአግባቡ ለጥፎ የመጠቀም፤
12. ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ሕገ-ወጥ ባለሞተር ብስክሌቶችን የመከላከል ሥራ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ የመስራት፤

## 19.የሞተር ብስክሌት አሽከርካሪዎች ኃላፊነት

1. ተገልጋዩ ያለበትን ግዴታና መብቱን የማሳወቅ እና ተፈፃሚነቱን የመከታተልና የመቆጣጠር ግዴታ አለበት፤
2. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ፤ የኢትዮጵያ ደረጃ ጥራትና ንጽሕናውን የጠበቀ እንዲሁም ማሰሪያው በአግባቡ የታሰረ ቆብ ለራሱና ለሚያሳፍረው ሰው የማድረግ እና በቂ የደህንነት መጠበቂያ መደረጉን የማረጋገጥ፤
3. ዝቅተኛ ፍጥነት ባለበት የትራፊክ ፍሰት የሞተር ብስክሌት አሽከርካሪ በተለየ ፍጥነት አለማሽከርከር፤
4. የክልሉ ትራንስፖርት መዋቅር የሚያዘጋጀውን መንቀሳቀሻ ፈቃድ፣ የደረት ባጅ፣ የደንብ ልብስ ሳያደርግ አለማሽከርከር፤

## 20. የሞተር ብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት ማህበራት እና ድርጅቶች ኃላፊነት

1. ሠሌዳ ያላቸው የሞተር ብስክሌት ባለንብረቶች በማህበር ከተደራጁ በኋላ አዲስ ወደ ማህበር የሚገቡ ሞተር ብስክሌቶች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው ደረጃ መሠረት የተመረቱ ሞተር ብስክሌት መሆናቸውን አረጋግጠው ይመዘግባሉ፤
2. በማህበሩ የሚደራጁ ሞተር ብስክሌቶችን ከመመዝገባቸው በፊት ከመንግስት የሚጠበቅባቸውን አስተዳደራዊ እና ቴክኒካዊ ጉዳዮች ማሟላታቸውን ያረጋግጣሉ፤
3. ማናቸውም በማህበር የተደራጀ የሞተር ብስክሌት ባለቤት ወይም ተወካዮቻቸው ስራዎችን በመገምገም በትራንስፖርት አገልግሎት የታዩ ያልተገቡ ተግባራትን ማረም
4. በሞተር ብስክሌታቸው ወይም በማህበራቸው የተፈጸሙ ወንጀሎች ካሉ ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፤
5. የመንገድ ደህንነትን የሚከታተል ክፍል ማቋቋም አለባቸው፤
6. የሞተር ብስክሌት ተሽከርካሪዎች የህዝብ ማመላለስ አገልግሎት ላይ የሚሰማሩበትን የስምሪት መርሀ-ግብር ትራንስፖርት ቢሮው በሚያወጣው መስመር መሰረት ማውጣት፤
7. የሞተር ብስክሌት አሽከርካሪዎች በጀርባ በኩል በጉልህ የሚታይ መለያ ቁጥር ወይም የሞተሩ ሰሌዳ ቁጥሩ የታተመበት የደንብ ልብስ እንዲለብሱ እና 10 በ 20 ሳንቲ ሜትር ባጅ ማድረጋቸውን ማረጋገጥ፤
8. የኦፕሬተር ፍቃድ የሚቀየር ከሆነ ሥራ ከማቆሙ ከ15 ቀን በፊት የብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ለሰጠው አካላ ማሳወቅ፤

9. አግባብነት ካለው አካል በልዩ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ማህበር እና ድርጅት ከተፈቀደለት የሞተር ብስክሌት ተሸከርካሪዎች ዝርዝርና ብዛት ውጭ አለማሳተፍ፤

10. ለአገልግሎት የሚውሉ የሞተር ብስክሌት ተሸከርካሪዎች የ3ኛ ወገን መድን ሽፋን ያደሰ መሆኑን ሳያረጋግጥ ስምሪት መስጠት የለበትም ፤

11. ተጠቃሚው ፈቃድ ሲያገኝ በሰጠው አድራሻ መሠረት ለማንኛውም ጉዳይ ክልሉም ሆነ በሚመለከተው አካል ሲፈለግ የመቅረብና የአድራሻ ለውጥም ካደረገ የማሳወቅ ኃላፊነት ይኖርበታል፤

12. በተቆጣጣሪ አካላት ስለማህበር አባሎቻቸው መረጃ ሲጠየቁ የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡

**21. የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ እና የመቆጣጠሪያ ስርዓት ቴክኖሎጂ (GPS) አቅራቢ ድርጅቶች ኃላፊነት**

1. **የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂን እና የመቆጣጠሪያ ስርዓት ቴክኖሎጂ (GPS) የሚያቀርበው ተቋም በሀገሪቱ የንግድ ህግ መሠረት የተመዘገበና የታደሰ ፈቃድ ያለው እንዲሁም ከቢሮው ጋር የግዴታ ውል መግባት የሚችል መሆን አለበት፤**
2. **የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂን እና የመቆጣጠሪያ ስርዓት ቴክኖሎጂ (GPS) የሚያቀርበው ተቋም የሀገሪቱን የመረጃ ደህንነት ጠብቆ የሚሰራ መሆን አለበት፤**
3. **የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂን እና የመቆጣጠሪያ ስርዓት ቴክኖሎጂ (GPS) የሚያለማው ተቋም ለቢሮው ማንኛውንም የሞተረኛ መረጃ ማቅረብ የሚችል መሆን ይገባዋል፤**
4. **የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂን እና የመቆጣጠሪያ ስርዓት ቴክኖሎጂ (GPS) የሚያለማው ተቋም ከሞተር ተጠቃሚ ጋር በተያያዘ የሚያገኘውን ማንኛውንም መረጃ ከውሉ ውጭ መጠቀም አይችልም፤**
5. **መከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂን እና የመቆጣጠሪያ ስርዓት ቴክኖሎጂ (GPS) የሚያለማው ተቋም ከሞተር ተጠቃሚ ጋር በተያያዘ የሚያገኘውን ማንኛውንም መረጃ ቢያንስ ለአንድ ዓመት መያዝ የሚችል የመረጃ ቋት በአገር ውስጥ ሊኖረውና ሙሉውን መረጃ ለቢሮው በተፈለገው ጊዜ ማቅረብ የሚችል መሆን ይገባዋል፤**
6. **ውል ያስገባውን የሞተር ብስክሌት ተጠቃሚ በውሉ መሠረት መቆጣጠር ካልቻለ ውል የገቡ ተጠቃሚዎችን ያለምንም ተጨማሪ ክፍያ ወደ ሌላ በቢሮው እውቅና ለተሰጠው ተቋም ያዛውራል፤**
7. **ቢሮው የሚፈልጋቸውን መረጃዎች ሁሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በተጠየቀ ጊዜ ሁሉ ማቅረብ ይኖርበታል፤**
8. **በገባው ግዴታ መሠረት ለቢሮው መቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂውን እና የመቆጣጠሪያ ስርዓት ቴክኖሎጂ (GPS) የማየትና መረጃ የማግኘት መብት መስጠት፤**
9. **የመጠቀሚያ ፈቃዱን በወቅቱ የማደስ፤**
10. **የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂ ከመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ ጋር ሳይገጥሙ በክልሉ እና በከተማው የተለያዩ ቦታዎች ላይ አለመንቀሳቀስ፤**
11. **በቢሮው ፍላጎት መሰረት በየትኛውም ጊዜ በመቅረብ ተገቢ መረጃ መስጠት፤**

12. የተገጠመውን የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ከቢሮው እውቅናና ፈቃድ ውጪ ከተገጠመበት ቦታ አለመቀየር፤
13. በማንኛውም ሁኔታ የተገጠመውን የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ አለማጥፋት ወይም አለማበላሸት።
14. የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ቴክኖሎጂው ሁልጊዜ ስራ ላይ መሆኑን ማረጋገጥ፤
15. ከሞተር ብስክሌት ተጠቃሚዎች ጋር ውል ሲገባ በዚህ መመሪያ የተፈቀደውን የፍጥነት ወሰን አክብሮ እንዲንቀሳቀስ ግዴታ ያስገባዋል፤ ከፍጥነት ወሰን በላይ ሲያሽከረክርም ምልክት ለቢሮው እንደሚሰጥ በማድረግ ሊያሳውቀው ይገባል፤
16. የተገጠመው የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ቴክኖሎጂ ላይ ብልሽት ሲያጋጥም ብልሽቱን በፍጥነት ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ፤
17. በማንኛውም ሁኔታ የተገጠመውን የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ አለማጥፋት ወይም አለማበላሸት፤
18. የተገጠመውን የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ከቢሮው እውቅናና ፈቃድ ውጪ ከተገጠመበት ቦታ አለመቀየር፤
19. የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂ ዕቃዎች ላይ ያለውን መለያ ኮድ አለማጥፋት ወይም አለመቀየር፤
20. እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር ከሚያስችለው ስርዓት (System) ጋር የሚናበብ እና ስርዓቱ (System) ተቀባይነት ያለው የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጂን ብቻ መጠቀም።

## ክፍል አምስት

### ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**22. ክልከላ**

1. ማንኛውም የሞተር ብስክሌት ባለንብረት በሞተር ብስክሌት ትራንስፖርት ማህበር ሳይደራጅ ወይም በመስፈርቱ መሰረት ንግድ ፈቃድ ሳያወጣ አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም፤
2. ማንኛውም ባለንብረት ሕጋዊ የሞተር ብስክሌት ማሽከርከር ፍቃድ ላልያዘ አሽከርካሪ ሞተር ብስክሌቱን አሳልፎ መስጠት የተከለከለ ነው፤
3. ማንኛውም የሞተር ብስክሌት አሽከርካሪም ሆነ ተጠቃሚ አስፈላጊውን የአደጋ መከላከያ ቆብ በአግባቡ ሳያደርግ ወይም በአግባቡ ማድረጉን ሳያረጋግጥ በገጠርም ሆነ በከተማ መንገዶች ላይ ማሽከርከር የተከለከለ ነው፤
4. በአካባቢው ሥሌዳ ለሌላቸው ባለሞተር ብስክሌቶች ሥሌዳ መስጠት ከተጠናቀቀ በኋላ ማንኛውም ማኅበር ሰሌዳ የሌለውን ባለሞተር ብስክሌት በማኅበር አባልነት መመዝገብ የተከለከለ ነው፡፡

**23. ስለ ቅጣት**

1. **በሌላ ሕግ የተጣሉ ቅጣቶች እንድተጠበቁ ሆኖ በዚህ መመሪያ የተከለከሉ ተግባራትን የፈፀመ የሞተር ብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጭ አሽከርከሪ በጥፋቱ አይነት ቅጣት ይጣልበታል፤**
2. **የጥፋት አይነት፣ በደረጃ እና እንደጥፋቱ ክብደት የሚጣሉ ቅጣቶች በግልፅ መቀመጥ ይኖርባቸዋል።**

24. **ደረጃ አንድ የጥፋት አይነቶች** (500.00 ብር የሚያስቀጣ የጥፋት ዓይነት)

**ማንኛውም፡-**

1. **የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሞተር ብስክሌት አሽከርካሪ በመመሪያው መሰረት የተዘጋጀ የስራ ልብስ (ዩኒፎርም) በአግባቡ ያልለበሰ፤**
2. **የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሞተር ብስክሌት አሽከርካሪ የቆሸሸ፣ የተቀደደ፣ ይዘቱን ያልጠበቀ እና ጀርባው ላይ የሚቀመጠው ጹሁፍ ከርቀት የማይለይ የስራ ልብስ (ዩኒፎርም) ለብሶ ያሽከረከረ፤**
3. **በመመሪያው መሰረት ህጋዊ የሆነ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ኖሮት ሳይዝ ያሽከረከረ ወይም በወቅቱ ያላደሰ፤**
4. **በሚመለከተው አካል ከተቀመጠው የድምጽ ስታንዳርድ በላይ ሙዚቃ ከፍቶ ያሽከረከረ፤**
5. **በዚህ መመሪያ ከተፈቀደው የዕቃ መጫኛ ውጭ ዕቃ የጫነ፤**

**ከሆነ የ**500.00 **ብር ቅጣት ይጣልበታል።**

25. **ደረጃ ሁለት የጥፋት አይነቶች**(1000.00 ብር የሚያስቀጣ የጥፋት ዓይነት)

**ማንኛውም፡-**

1.**የሞተር ብስክሌት ትራንስፖርት አሰጣጥ ላይ የሚሰማራ ድርጅት ወይም ማህበር በዚህ መመሪያ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ሳይኖረው አገልግሎት የሰጠ፤**

2.**የተሰረዘ ወይም የተደለዘ ወይም ጊዜው ያለፈበት የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ይዞ የተንቀሳቀሰ፤**

3.**የሞተር ብስክሌት አገልግሎት ሰጪ ማህበር፣ ድርጅት ፈቃዱን አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ ለማሳየት ፈቃደኛ ያልሆነ፣**

4.**በትራንስፖርት ተቆጣጣሪ እንዲቆም ሲጠየቅ ለመቆም ፈቃደኛ ባለመሆን አምልጦ የሄደ፤**

5.**የተገጠመውን የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጅ በማንኛውም ሁኔታ በሆን ከቢሮው እውቅናና ፈቃድ ውጪ ከተገጠመበት ቦታ የቀየረ፤**

26. **ደረጃ ሦስት የጥፋት አይነቶች** (1500.00 ብር **የሚያስቀጣ የጥፋት ዓይነት**)

1. **በሥራ ላይ እያለ አግባብ ባላቸው የክትትል፣ የድጋፍና ቁጥጥር ሠራተኞች ወይም ሌሎች ሕጋዊ አካላት ማንኛውም ዓይነት መረጃ ሲጠየቅ ለማሳየት ፈቃደኛ ያልሆነ፤**
2. **አግባብ ካለው አካል ካልተፈቀደ በስተቀር የሞተር ብስክሌት ተሽከርካሪው ከተፈቀደለት የአገልግሎት ዓይነት ውጭ እንዲሠማራ በማድረግ የትራንስፖርት አገልግሎት አሠጣጥ ላይ የተገኘ እና አፈፃፀሙን ያዛባ፤**

27. **ደረጃ አራት የጥፋት አይነቶች** (2000.00 ብር **የሚያስቀጣ የጥፋት ዓይነት**)

**ማንኛውም፡-**

1. **በዚህ መመሪያ የወጣውን መመዘኛ ያላሟሉ በተለያዩ የዲሲፒሊን ጉድለት ምክንያት የተቀጡ እና የታገዱ የሞተር ብስክሌት አሽከርካሪዎችን የቀጠረ፤**
2. **የሞተር ብስክሌት አገልግሎት ሰጪ ማህበር፣ ድርጅት ፈቃዱን አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ ለማሳየት ፈቃደኛ ያልሆነ፤**
3. **የመጠቀሚያ ፈቃዱን በወቅቱ ያላደሰ፤**
4. **የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂ ከመከታተያ ስርዓት ቴክኖሎጅ ጋር ሳይገጥም በክልሉ ወይም በከተማው የተለያዩ ቦታዎች ላይ የተንቀሳቀሰ፤**

28. **ደረጃ አምስት የጥፋት አይነቶች**(4000.00 ብር **የሚያስቀጣ የጥፋት ዓይነት**)

**ማንኛውም የሞተር ብስክሌት አሽከርካሪ፡-**

1. **ህጋዊ ያልሆነ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ይዞ የተገኘ እና የተጠቀመ፤**
2. **የመንቀሳቀሻ ፈቃዱን ለሌላ አካል አሳልፎ የሰጠ፤**
3. **የመቆጣጠሪያ መሳሪያ** (GPS) **የነቀለ ወይም ከአገልግሎት ውጪ ያደረገ፤**
4. **የመቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂ ዕቃዎች ላይ ያለውን መለያ ኮድ ያጠፋ ወይም የቀየረ፤**
5. ለሞተር ብስክሌት ብቻ የተወሰኑ ኮሪደሮች ወይም መስመሮች በቋሚነት ወይም በተወሰኑ ሰዓታት እንዳይንቀሳቀሱ በተከለከሉ መንገዶች ገብቶ ያሽከረከረ፤
6. መንቀሳቀሻ ፈቃድ ሳይኖረው ያሽከረከረ፤

**29. ደረጃ ስድስት የጥፋት አይነት(**ለ3 ወራት የመንቀሳቀሻ ፈቃድ የሚያሳግድ የጥፋት ዓይነት)

ማንኛውም የሞተር ብስክሌት አሽከርካሪ፡-

1. የእንቅስቃሴ ክልከላ ወይም ገደብ በተጣለበት ወቅት ሲንቀሳቀስ ከተገኘ፤
2. ለሌላ ተሽከርካሪ የተሰጠ ፈቃድን እንደራስ አስመስሎ የተጠቀመ፤

## 30. አቤቱታ ስለማቅረብ

በዚህ መመሪያ መሠረት በተወሰደው እርምጃ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው፡-

1. እርምጃው በተወሰደ በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለሚመለከተው ቢሮ የበላይ ኃላፊ በፅሁፍ ማቅረብ ይችላል፤
2. የቢሮው የበላይ ኃላፊ አቤቱታው በቀረበለት በአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን መርምሮ ውሳኔ መስጠት አለበት፤ ውሳኔውንም በጽሁፍ አድርጎ ለአቤቱታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት፤
3. አቤቱታ አቅራቢው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልተሰጠው ወይም በተሰጠው ውሳኔ ቅር ከተሰኘ አግባብ ላለው አካል ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።

## 31. የመተባበር ግዴታ

ይህንን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የትራንስፖርት ድርጅቶች፣ ማህበራትና ግለሰቦች የመተባበር ግዴታ አለባቸዉ፡፡

## 32.ተፈጻሚነት የማይኖራቸዉ ህጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛዉም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረዉም፡፡

## 33. መመሪያዉን ስለማሻሻል

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሚኒስቴሩ ይህን መመሪያ ሊያሻሽለዉ ይችላል፡፡

## 34. መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ


ይህ መመሪያ ከ …… ቀን /2017 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ዶ/ር ዓለሙ ስሜ**

**የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚንስቴር ሚኒስትር**

## 35.አባሪ ሰነዶች

1. የባለሞተር ብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጭ ማህበራት እና ድርጅቶች ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ
2. የባለሞተር ብስክሌት ትራንስፖርት ሰጭ ማህበራት እና ድርጅቶች ሞዴል የኦፐሬተር ፍቃድ ፎርም
3. የባለሞተር ብስክሌት ትራንስፖርት ሰጭ ማህበራት እና ድርጅቶች እንዲሁም ለግል አገልግሎት የሚጠቀሙ ግለሰቦች መመዝገቢያ ፎርማት
4. የባለሞተር ብስክሌት ትራንስፖርት ሰጭ ማህበራት እና ድርጅቶች ሞዴል መንቀሳቀሻ ፈቃድ
5. በጥፋተኝነት ክስ ወረቀት ላይ ሊሞሉ የሚገቡ መረጃዎች፡-


Ministry of Transport and Logistics/የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር
Road Traffic Violation Receipt/የትራፊክ ቅጣት ደረሰኝ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| Region of/ክልል | city of/ከተማ | | Agency Name/ኤጀንሲው ስም | | Receipt Number/የደረሰኝ ቁጥር--------- |
| day of week/ሳምንት | Month/ወር | Day/ቀን | Year/ዓ.ም | Time/ሰዓት | □ A.M/ጠዋት □ P.M/ከሰዓት |
| Name/ስም | | Middle/የአባት ስም | | Last/የአያት ስም | |
| Region ክልል | Subcity/Zone/ ክ/ከተማ | Woreda/ ወረዳ | House number/ የቤት ቁጥር | Tel.Number/ ስልክ ቁጥር | |
| Date of Birth የትውልድ ቀን | Month/ወር | Year/ዓ.ም | Sex/ጾታ □ Female/ሴት □ Male/ወንድ | City/ከተማ | |
| Driving Licence Number የመንጃ ፈቃድ ቁጥር | State/የሰጠው አካል | Grade/ደረጃ | Yr. Licence Exp. መንጃ ፈቃዱ የሚያበቃበት ቀን | | |
| Vehicle Plate No. የመለያ ቁጥር ሠሌዳ | Trailer Plate no የተሳቢ የመለያ ቁጥር ሠሌዳ | Make/ስሪት | Style/አይነት | Color/ቀለም | |
| Commercial Vehicle የጭነት ማመላለሻ ተሽ. □ | Passenger Vehicle የህዝብ ማመላለሻ ተሽ.□ | Automobile አውቶ ሞቢል □ | Motorcycle ሞተርሳይክል□ | Tricycle ባለሶስት እግር ተሽከርካሪ □ | Other ሌላ □ |
| Violation Occurrence location/ደብን ጥሰት የተፈጸመበት ቦታ | | | | | |
| Region/ክልል | City/ከተማ | Sub city/zone/ክ/ከተማ | Special location/ልዩ ቦታ | | |
| commit the following offence/የተፈጸመው የደንብ ጥሰት ------------ category of offence/ ደረጃ------------- | | | | | |
| Other offence/ ሌላ የተፈጸመ ጥፋት-------------------------- | | | Comments Pertaining to the offence/ ስለ ተፈጸመው ጥፋት አስተያየት---------------- | | |
| Crash/ግጭት □ | Property damage/የንብረት ጉዳት □ | Injury to another/የአካል ጉዳት □ | Fatal/የሞት አደጋ □ | | |
| Criminal violation/የወንጀል ተግባር □ | Arrest/በቁጥጥር ስር መዋል □ | Licence surrendered/መንጃ ፈቃድ ተይዟል □ | | | |
| Name officer/የትራፊክ ስም | | ID number/መታወቂያ ቁጥር | | Signature/ፊርማ | |

Warning: failure to sign may lead to your arrest.

ማስጠንቀቂያ፡ ይህንን የቅጣት ወረቀት አለመፈረም በቁጥጥር ስር መዋልን ያስከትላል

I sign my name as evidence of receipt of a copy of this charge and not as an admission of guilty. I will comply with the requirements.

ይህንን የቅጣት ደረሰኝ መፈረም ጥፋተኛነትን ማመን አይደለም።

Signature /ፊርማ

## 36.ስለ ተጠያቂነት

ክልሎች ሰነድ አልባ ባለሞተር ብስክሌቶችን ወደ ሕጋዊ መስመር ለማስያዝ የትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር እና የጉምሩክ ኮሚሽን ከሚያወጡት የመጨረሻ ዕለት ድረስ ማንኛውም ሠሌዳ አልባ ባለሞተር ብስክሌት ህጋዊ ሂደቱን ሳያልፍ ሰሌዳ አልባ ሞተር ሳይክል ይዞ ቢገኝ በህገወጥ ንብረት በመጠቀሙ ምክንያት አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

ያለ መንጃ ፈቃድ ባለሞተር ብስክሌት ሲያሽከረክር የተገኘ አሽከርካሪ ከመንገድ ትራንስፖርት ሕጎች ቅጣት በተጨማሪ በወንጀል ሕግም እንዲጠየቅ ይደረጋል፡፡ ነገር ግን በክልሎች ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት በማድረግ የመንገድ ደህንነት እና መድን ፈንድ ጥናቶች በማድረግ እና የክልሎችን ዝርዝር እና ቀነ ገደብ በማውጣት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ የሌላቸውን እና የማሽከርከር ችሎታ ያላቸውን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ እንዲያገኙ ሊያደርግ ይችላል፡፡